<u>ለእናቶች ለእህቶች</u>

ያኔ ዓለም ሲከሰት ከነግሳንግሱ

ዘፌኑ ቀረርቶው ምስጋናው ታሪኩ

ለአዳም ሆኖ ሁሉ

አመጣጧ ግራ የአጥንት ህልውና

ሐጢያት አስተናጋጅ ሳትጠና ገና

ሔዋን እናታችን ከዚያኔው ተወግዛ

ከያኔው ተሰድባ

ሚነበብ መፅሀፍ ቅድሱ ቁራኑ

ዝቅተኛ ብሏት፤ለአዳም ተገዢ፤ምክንያት ለውድቀቱ ::

ለባሏ መገዛት የሴት ልጅ  ዘውድነት

ዋጋ ወርቅነቷ ከሎሌነት ሚሰርፅ

ርግማን ተቀባይ ገና ስትረገዝ

ለሽያጭና ሞት ታጭታ ምትጠበቅ ::

ቻይና አልን አፍሪካ ህንድ ሆነ በአረቦች

መከራቸው ብዙ ሁሉም እናት እህቶች

ስቃያቸው መዓት የዚህ ዓለም ሴቶች::

---

አንጎሉ ችሎታው ብቃቱ ሳያንሳት

ባህል ሃይማኖቱ ዕድሏን ቀምቷት

በዝባዦች ገዢዎች ባሎችና ወንዶች

አፍነው ይዘዋት

ውድ እናት እህቴ ጭቆናዋ በዝቶ

ድርብ ደግሞ ድርብ እጅና እግሯ ታስሮ

ገና ስትወለድ ታፍና እየሞተች

በዱር በገደሉ ለአውሬ እየተጣለች

ትደግ ከተባለም ተዳርጋ ለወፍጮ

ለሸክም ለእንስራ

የመማር ዕድሏን በአብዛኛው ተነፍጋ

ህፃን አካላትዋ ለአቅመ ሔዋን ሳይደርስ

ለጨቋኝ ተድራ ተደፍራ ምታለቅስ

ስትቆረጥ ለቅሶ ስትሸለት ለቅሶ

ስትገረዝ ለቅሶ ስትረገጥ ለቅሶ

ሁሌም ለቅሶ ስቃይ የመከራ ኑሮ
ወንዱም ልበ ክፉ ላይማር ደንቁሮ፡፡
የወር አበባ እንኳን ያውም የተፈጥሮ
ካ ጢያት ተፈርጆ
ለቆሻሻነቷ፤ልዩ ለመሆኗ ምልክት ተብሎ
አባት ሚሆናትን ቢያንስም ታላቅ ታላቅ
ማግባት የግድ ሆኖ
እምቢታም ቢከጀል ጠለፋውም ደርቶ
ህፃን ልጅ ጭቁኗ ህፃኑን አርግዛ
ወሊድ ቁጥጥሩን በህግ ተከልክላ
ወሊድን ማለፉም የአንድ በአምስት ዕጣ
ከማጀት ወደ እርሻ ከእርሻ ወደ ማጀት
ፍዳ ኑሮን መግፋት ተቆጥሮ ከሕይወት
ጭቃ ሹም ሻምበሉ ካድሬውም አዞባት
ማርያምን ሚርደው በእሷ ግን ነግሶባት
ህጉም ቁምጣ ለባሽ ለወንድ የሚያደላ
ለእስር ሚዳርጋት ሴቲቷ ተደፍራ፡፡
ሴት ሆኖ መወለድ የስቃይ ሰለባ
የሀገራችን ግፍ መቾም ማያባራ፡፡
ነብርን በጫንቃ አዝሎ ወርቂቷን በጭቃ
እህትንም ንቆ፤ እናትንም ንቆ አጉል ክብር ፍለጋ፡፡

ዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐዐ

ሆድ ይፍጀው ይቅርና እስቲ እንነጋገር
ገበናው ይሰጣ አንዲት ቅንጣት ሳይቀር
ሴት ልጅ ምን ባጠፋች ይኸ ሁሉ በደል
ገላዋን መቁረጡ ስትወለድ መግደል?
የህፃን ሳቅ ለቅሶ ከልክሎ ማስለቀስ?
የት ላይ ነው መውደዱ የት ላይ ነው ማፍቀሩ
ልጅን አሳልፎ ለባዳ እየሰጡ
ለከፋ ባርነት ለአረብ እየላኩ?
ለአቅመ ሔዋን ሳትደርስ በሰው ካስደፈሩ?
ወንጀልንም ትዳር ብለው ከደበቁ?
እስቲ እንነጋገር ምንም ሳይሸፈን
ሴት ልጅ ምን ባጠፋች ይኸ ሁሉ በደል?

ዘጠኝ ወር አርግዛ አምጣ ምትወልደው
የተፈጥሮን ጥበብ በማህፀኗ ይዛ ውበት የምትስለው
ሴቷ ልጅ እንጂ ናት መች ደንፊው ወንዱ ነው።
የሴት ልጅ ይላሉ ግርማ ሞገሰ ክብሩን ከስድብ ፈርጀው
መሳቂያ እየሆኑ ድንቁርናን አቅፈው
እናት ተኪ የለሽ የፍቅር ጎተራ
የሁሉም ማንነት ከየት የመጣ ነው ከእሷ ካልሆነማ?
እናቱን ከናቀ እሱ ማን ሊባል ነው
ማን ሆኖ ሲወለድ ህይወት የለገሰው?
የሁሉም እናቶች የኛ ሁሉ እህቶች
ሁሉም ዕንቁ ሴቶች
ሆነው ሳለ ክቡር ላገር ምሰሶዎች
ይናቁ የለም ይባሉ የለም ወይ ዝቅተኛ ዜጎች?
መገለል ዕጣቸው መጨቆን ኑሮአቸው
ማነው ይህን ሁሉ የፈረደባቸው?
እስቲ እንነጋገር ገበናው ይሰጣ
ማነው ሀገር ገንቢ ማነው ቆራጥ ጀግና?
ማነው መጠለያ ለስንቱ ደካማ?
ታሪክ ነው ተረት ነው ወንዱ ብቻ ጀግና
ላገሩ የሞተ ብሎ የሚያወሳ
የሴቶችን ሚና ከቶም ማያነሳ?
ሀቅ ነው  ውሸት ነው ሴት ልጅ ፈሪ ብሎ የሚለፈልፈው
የወንዱ ጀግንነት የሴቷ ፅንስ ሆኖ
የእነ አቶን ፍርሀት ሴቱ እያሸነፈው?

ዘመን ተለውጦ አንበሳ ሳይገድሉ ጎፈሬ ጉትቻ
ታሪክን ፀሀፊው ሆኖ ወንዱ ብቻ
መወድስ ራሴን ሲጠርቅ ሲደልቅ
የሴቶችን ሚና ሲያንኳስስ ሲያናንቅ
ዘመን አለፈና ትምክህትም ጌጥ ሆኖ
የሴቶች ጭቆና ሁሉንም ተብትቦ
ህብረተሰብ ሁሉ በዚህ ምክንያት ታሞ
ደፋ ቀናው ቀጣይ ጭቆናው እስካለ

ዕድገት ኬት ሊመጣ ሴት ከተጨቆነ
እናቱን እህቱን ወንዱ ከበደለ ።
ይነገር ይታወቅ ገበናው ይሰጣ
በሴት በዳይ ሀገር ነፃነት አይመጣ!
ወንዶች ምኒሊኮች በአድዋ አሸነፉ
ወይስ ጣይቱዎች ከጎን ሆነው ታግለው ድልን አበሰሩ?
ዘመቻ የጥንቱ፤ የትላንት የዛሬው የመንግሥት የፋኖው
ሴት ልጅ ባትኖርበት ምን ነበር ሚውጠው?
የወንድ ወኔ ሚሉት ምንጩ ከወየት ነው
ሴት ልጅ ጀግናይቷ አምጣ ባትወልደው?
ደካማዋስ ማነው ጠንካራውስ ማነው
ግማሽ ሰማይ ይዞ ምስሶ የሆነው?
ግራዚያኑ ነጩ ግራዚያኑ ጥቁሩ
ባንዳ የትላንቱ  የዛሬም ሹምባሹ
ሀገርን ሲያደሙ ፍጅት ሲያካሂዱ
ሰለባ ወንድ ብቻ ወይስ ነበር ሴቱ?
አወቅን ነቃን ብለን ፋኖ ገቢ ጫካ
ቤቱን ማን አቆየች መቀነት አጥብቃ?
አረመኔው ደርጉ መሀይሙ ካድሬ ሲጫወት በሬሳ
በሯ ላይ ተሰጥቶ የማህፀኗ ፍሬ ደስታዋ ኩራቷ
ቀብርም ተከልክላ ------ እንባም ተከልክላ
ማናት ጀግናይቱ ፅንታና በርትታ ጠላት ያሳፈረች
የሁላችን እናት ያቺ ሴቷ እኮ ነች።
ታዲያ ጀግና ማነው ጠመንጃ አንግቦ ዱር ጫካ የገባው
ወይስ ቤቷ ቀርታ የናጠጠን ፋሺስት የምትጋፈጠው?
በዚያ ክፉ ዘመን ዛሬም በአውሬ ጊዜ
ለእናቶች እህቶች የነበረ አባዜ
የሚያዩት አባዜ
ተነግሮ መቸ ሊያልቅ መቸስ ተሞክሮ
ታሪክ በሴት መፃፍ መቼ ተጀምሮ!